የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጳጉሜ 2001 ዓ.ም.

## መልካም አዲስ ዓመት 2002

## 2002 የተፋፋመ ፀረ ወያኔ ትግል ዓመት ይሁንልን

ላለፉት 18 ዓመታት አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር ዕንቁጣጣሽ እንኳን ደህና መጣሽ ደስታ ተኖ በሀዘን እየተቀየረ ዜጋ ሁሉ መጪውን የስቃይና የተባባሰ መከራ ዓመት በጭንቀት እያሰበ ሲያሳልፍ ቆይቷል፡፡ የዛሬው የ2002 ዓመት መጀመሪያ ደግሞ ካለፈው በባሰና ወደሚብስም ሁኔታ እንደገባንና እንደምንገባ ግልፅ ያደረገ ነውና የመልካም አዲስ ዓመት ምኞታችን የተፋፈመ ትግል ዓመት ይሁንልን በሚል መታጀቡ የግድ ነው፡፡

በ2001 የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለፈው ዓመት በከፋ ሁኔታ ውስጥ መግባቱ ይታወቃል፡፡ ብዙሁኑ ዕልህ አስጨራሽና ተፈታታኝ በሆነ ድህነት ውስጥ ሲዘፈቅ፣ ከ 14 ሚሊዮን ያላነሰው በረሀብ ሲጠቃ፣ ከ 35 ሺ ያላነሱ የፖለቲካ እስረኞች በቀጣይ ስቃይ ሲጠበሱ ፣ በከተሞች እንኳን መብራትና ንፁህ ወይም በቂ ውህ ጠፍቶና የጤና ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተቃውሶ መቶዎች ወያኔ ሊደብቅው በሚጥረው በኮሌራ በሽታ ሲሞቱ፣ የሀገር ህልውና ለአደጋ ሲጋለጥ፣ ፍጅት በየአቅጣጫው በሕዝብ ላይ ሲፈፀም አይተናል፡፡ በአንፃሩ ፀረ ወያኔው ትግል በመፋፋም ፈንታ ቀዝቀዝ ብሎና ተቃዋሚ የተባሉትም ክፍሎች ሚናቸውን በሚገባ መወጣት አቅቷቸው ሲዳከሙ ታዝበናል፡፡ በስልጣን ያለው አረመኔና ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን በደደቢቱ የክፍፍል መርሀ ግብሩ መሰረት ሕዝብን እየከፋፈለና እያናከሰ ፣ሀገሪቷን እስከ አጥንቷ እየጋጠ በዘረኛ መንገዱ ሊጓዝ ቆርጦ ተሰይሟል፡፡ የሀገራችንን መሬት ለባዕድ አሳልፎ መስጠት ብቻ ሳይሆን በአባይ ወንዝ ያለንን መብትም ሸጧል፡፡ የሰብዓዊ መብት ረገጣው ተባብሷል፡፡ ግፍ ሞልቶ ተርፎ ፈሷል፡፡

ʾRP
.O.Box 73337
'ashington DC, 20056
SA
l. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

በዚህ ሁኔታ 2002 ዓመትን ስንቀበል የግድ የተፋፋመ ትግል ዓመት ያድርገው በሚል መሆን አለበት። ሕዝብ ሊቀበልና ሊሸከም የሚችለው በደልና ስቃይ ገደብ ሊኖረው ይገባልናም 2002 የእምቢ አልገዛም፤የበቃ! ዓመት መሆን አለበት። ለዚህም ሕዝብ የሚበጁትን የትግል መሪዎች፤ ቆራጥና ፅኑ የሆኑትን ለይቶ ከነሱና ከድርጅታቸው ዙሪያ መሰለፍ አለበት። ጎራውን ከአስመሳዮች ማፅዳት፤ ባንዳነትና ክህደት ከሚዳዳቸው፤ ከአገዛዙ ጋር በጥቅም ተሳስረው ትግልን ከሚያሸመደምዱ ማራቅ መለየት አለበት። 2002 ዓመት የተፋፋመ ፀረ ወያኔ ትግል ዓመት እስካልሆነ ድረስ 2003ንም በእንባና በሰቆቃ የምንቀበለው ይሆናል። እምቢ በቃ ብለን ለትግል እንነሳ! የወያኔን የምርጫ ቧልት ሆነ ሌላ አደናጋሪ ዘመቻ ሁሉ እናክሽፍ!

2002 የተፋፋመ የፀረ ወያኔ ትግል ዓመት ይሁንልን!!